# መጽሐፈ ኢያሱ (23)

## ጥናት አንድ (ኢያሱ ማን ነው?)

የጥናት ዓላማ፡ እግዚአብሄር እያንዳንዳችንን በዘመናችን ሊጠቀምብን ለሚፈልገው ነገር በተለያየ መንገድ እየሰራን ስላለ ከሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ ትምህርት ለመቅሰም እንድንሞክር ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡

1. ዘጸ 17፡8-14 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተካሄደው ነገር ምን እንደነበረ በአጭሩ በራስህ አነጋገር ለወገኖች ግለጽ፡፡
2. ቁ10 ‹‹ስለዚህ ኢያሱ ሙሴ ባዘዘው መሰረት ከአማሌቃውያን ጋራ ተዋጋ›› የዛሬ የኢያሱ ለሙሴ መታዘዝ ለወደፊት ህይወትና አገልግሎቱ ምን አስተዋጽዖ ይኖረዋል ትላለህ? ከዚህ ለህይወታችን ምን ልንማር እንችላለን?
3. ኢያሱ መስማቱን ሙሴ እርግጠኛ እንዲሆን እግዚአብሄር የፈለገው ሃሳብ ምን ነበረ? ለምንድነው ይህ ነገር አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው?
4. ዘጸ 24፡13-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የምታያቸውን ሰዎች አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡
5. ይህንን ክፍል ስታነብ ማን ነው ወደ እግዚአብሄር ተራራ የወጣው? በአንተ አመለካከት ወደ ተራራው ወጣ የተባለው ሰው ካልወጡት ሰዎች ምን የተለየ ነገር ይኖረዋል?
6. ለኢያሱ ይህ የተራራ ልምምድ ለወደፊት አገልግሎቱ ምን ይጨምርለታል/ይጠቅመዋል ትላለህ? 2ኛ ጴጥ 1፡16-18ን ማንበብ ይረዳል፡፡
7. ዘኁ 11፡26-30 ይነበብ፡፡ በዚህ ምንባብ ውስጥ እነማንን ታያለህ? ኢያሱን የምናየው ምን ሲያደርግ ነው? የተናገረው በሙሴ ዘንድ ምን ያህል ተቀባይነት ነበረው?
8. ኢያሱ ዛሬ ተሳስቶ በሙሴ መታረሙ፤ ከፊቱ ለሚጠብቀው ትልቅ ሃላፊነት የተሻለ አገልጋይ ለመሆን በምን መንገድ ሊረዳው ይችላል ብለህ ታስባህ?
9. ጦርነት ወደ ልዑል አምላክ እጅን የመዘርጋት ነገር መሆኑ፤ እግዚአብሄር በሚገኝበት ሥፍራ ጊዜ ማሳለፍና መሳሳት ሊኖር እንደሚችልና ከሌሎች ለመማር ክፍት የመሆን ነገር ከፊትህ ላለው መንፈሳዊ ህይወት አስፈላጊነቱ ምን ያህል ገብቶሃል? አንተም እግዚአብሄር ለአገልግሎቱ ሊያዘጋጅህ በህይወትህ እየሰራ ያለው ነገር እንዳለ ልትገነዘብ ያስፈልግሃል፡፡

# ጥናት ሁለት (ኢያሱ 1፡1-9)

የጥናት ዓላማ፡ እግዚአብሄር መከናወን የሚለው፤ እኛ ቃሉን በማንበብ፤ በማሰላሰልና በመታዘዝ ስንኖር እርሱ ደግሞ በመውጣት በመግባታችን አብሮን የመሆኑ ምሥጢር እንደሆነ ለመማር፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ይህ የህግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፤ በውስጡ የተጻፈውን ሁሉ በጥንቃቄ እንድትፈጽመውም ቀንም ሆነ ሌሊት ከሃሳብህ አትለየው፤ ይህንን ካደረግህ ያሰብከው ይቃናል፤ ይሳካልም፡፡›› ኢያሱ 1፡8

1. ኢያሱ 1፡1-9 በአንድነት ይነበብ፡፡ በመጀመሪያዎቹ አምስት ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር ለኢያሱ የተናገራቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡
2. በሙሴና በኢያሱ አገልግሎት አጀማመር መካከል የምታያቸውን ግንዛቤዎች ተናገር፡፡
3. ዘዳ 32፡8 እስራኤል ሁሉ ለሙሴ ሞት ሰላሳ ቀን አልቅሰዋል፡፡ ታዲያ በዚህ ክፍል ለምንድነው አግዚአብሄር የሙሴን መሞት ጫን አድርጎ ለኢያሱ ማረጋገጥ የፈለገው?
4. ዘዳ 11፡24-25 እና ኢያሱ 1፡3-4 ይነበብ፡፡ ‹‹…እግራችሁ የሚረግጠውን ቦታ ሁሉ እሰጣችኋለሁ›› ሲልና ከታች ደግሞ የርስታቸውን ክልል መንገሩ ለአዕምሮው ጥያቄ ለሚፈጥርበት ሰው እንዴት ብለህ ታስረዳለህ?
5. ቁ6 ‹‹ለቀደሙት አባቶቻቸው እሰጣችኋለሁ ብዬ የማልኩላቸውን ምድር…›› ይህ ተስፋ ከተገባ በግምት ስንት ዓመት ይሆነዋል? አንተስ የእግዚአብሄር ተስፋ እስኪፈጸም ስንት ዓመት መታገሥ ትችላለህ? ዕብ 11፡39
6. በዚህ ክፍል እግዚአብሄር ለኢያሱ እየሰጠ ያለውን የጦር ስልት ሌላ ምድራዊ የጦር አማካሪ ሊሰጥ ከሚችለው ምክር በምን መንገድ የተለየ ሆኖ ታየዋለህ? መሳካትንና መከናወንን ከምን ጋራ ነው እግዚአብሄር ያገናኘው?
7. አትፍራ አትደንግጥ የሚያሰኙ ኢያሱን ሊያስፈሩት የሚችሉት ምን ነገሮች ይታዩሃል?
8. በዛሬው ምንባብ መሰረት ለፍርሃት መልስ/መድሃኒት ሆኖ የቀረበው እውነት ምንድነው? አንተስ የሚያስፈሩ ነገሮች ሲገጥሙህ መልስህን ከየት ትፈልጋለህ?
9. የእግዚአብሄርን ቃል ማጥናትንና በህይወት መከናወንን ማገኘትን ምን ያህል አዛምደህ ታያቸዋለህ? ያለቃሉ መከናወን ስለሌለ በህይወት በቂ ትኩረት ለመስጠት ትጋ፡፡

# ጥናት ሶስት (ኢያሱ 1፡10፡18)

የጥናት ዓላማ፡ ክርስትና በራሳችን ድል ብቻ ረክተን እፎይ የምንልበት ህይወት እንዳልሆነና እንደ እግዚአብሄር ሰራዊት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከጎናችን የተሰለፉትን የወንድሞቻችንና የእህቶቻችን ጦርነት የምንዋጋበት ህይወት እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹…እናንተም ከወንድሞቻችሁ ጎን ተሰለፉ፡፡ ይህም እግዚአብሄር እስኪያሳርፋቸውና ለእናንተም እንዳደረገው ሁሉ እነርሱም እግዚአብሄር አምላካችሁ የሰጣቸውን ምድር እስኪወርሱ ድረስ ነው፡፡›› ኢያሱ 1፡14-15

1. ኢያሱ 1፡10-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ10-11 መሰረት ኢያሱ ህዝቡ እንዲሰሙት የፈለገው ነገር ምን ነበረ? ማን ነበረ መልዕክቱን ለማድረስ ሃላፊነት የተቀበለው?
2. እግዚአብሄር በ1፡1-9 ባለው ክፍል ኢያሱን ያበረታታበትና ያነቃቃበት ነገር ሰርቶለታል ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን?
3. በቁ11 ሲታይ ኢያሱ አንድ የተረዳው ትልቅ እውነት እንዳለ ይታያል፡፡ ይህ እውነት ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
4. ለምንድነው ኢያሱ ለሮቤል፤ ለጋድና፤ ለምናሴ ነገድ እኩሌታ የተለየ አይነት ትዕዛዝ መስጠት የነበረበት?
5. ቁ13 ትንና 15 ስናይ ኢያሱ ሙሴ የወሰናቸውን ውሳኔዎች ሲያጸና እናነባለን፡፡ ከዚህ አይነቱ አሰራር ልንማር የምንችለው ነገር ምንድነው?
6. በቁ12-18 ትን ስናነብ ለሁለት ተኩሌቹ ነገዶች ኢያሱ የሰጠው መመሪያ ምን ነበረ? እነርሱስ የተሰጣቸውን መመሪያ የተቀበሉት በምን ዓይነት መንገድ ነበረ?
7. ዘኑ 32፡6-10 ከሰፈረው ሃሳብ ጋራ በማነጻጸር ስንመለከተው የእነዚህ ሁለት ተኩል ነገዶች አብሮ ከወንድሞቻቸው ጋራ መውጣት ለወንድሞቻቸው በምን መንገድ ጠቃሚ ይሆናል ትላለህ? ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ ባይሆኑስ እግዚአብሄር ድርጊታቸውን እንዴት ያየዋል?
8. አስፈላጊ በሆነው ሁሉ ከክርስትያን ወገኖች ጎን መሰለፍ በህይወታቸው ተስፋ እንዳይቆርጡና እንዲበረታቱ እንደሚረዳቸው ከቃሉ ተምረናል፡፡ ይህንን ትምህርት በመማርህ በአመለካከትና በአኗኗርህ ምን ለውጥ ታደርጋለህ? በሳምንቱ ውስጥ አብሮት የሚቆም ሰው የሚያስፈልገው ሰው በማሰብ ጌታ ያስተማረህን ትምህርት በሥራ ተርጉመው፡፡

<u>ጥናት አራት (ኢያሱ 2፡1-24)</u>

የጥናት ዓላማ፡ ትናንትና መሻገር የማይቻለውን ያሻገረን እግዚአብሄር ዛሬም ከፊታችን የተጋረጠውን መከራ በድል ሊያሳልፈን የታመነ አምላክ እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡‹‹ከዚህ በኂላ ሳሙኤል አንድ ድንጋይ ወስዶ በምጽጳና በሼን መካከል አቆመው ስሙንም እግዚአብሄር እስከ አሁን ደረስ ረድቶናል ሲል አቤንኤዘር ብሎ ጠራው፡፡ 1ኛ ሳሙ 7፡12

1. ኢያሱ 2፡1-24 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-3 ባለው ክፍል እነማንን ታያለህ? ለምንድነው የሰላዮቹ ተልዕኮ ስውር እንዲሆን ኢያሱ የመረጠው?
2. በቁ9-10 መሰረት ረዓብ አውቃለሁ በማለት ለሰላዮቹ የነገረቻቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
3. ቁ11 ‹‹ይህን በሰማን ጊዜ ልባችን ቀለጠ›› ይላል፡፡ የኢያሪኮን ህዝብ ልቡን ያቀለጠው ነገር ምን ነበረ?
4. ቀይ ባህርን የከፈለላቸው ከአርባ ዓመታት በፊት ሲሆን የአሞራዊያንን ነገሥታት ድል ያደረገላቸው ደግሞ በቅርቡ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ድሎች የእስራኤል ህዝብ ስለ እግዚአብሄር ታማኝነት ምን ሊማር ይገባዋል ትላለህ?
5. ቁ11 ‹‹ይህን በሰማን ጊዜ ልባችን ቀለጠ›› ስለ እግዚአብሄር የኢያሪኮ ህዝብ ከትልቁ እስከ ትንሹ ሰምቷል፡፡ የረዓብን መስማት ልዩ የሚያደርገው ምንድነው? ከዚህ ምን መማር እንችላለን?
6. 1፡11 ትንና 2፡14 ትን ስናነብ ኢያሱና የተላኩት ሁለት ሰላዩች መካከል የአመለካከት ተመሳሳይነትን እናያለን፡፡ ይህ በሁለቱ መሃል የጋራ የሆነው አመለካከት ምንድነው?
7. በዘሁ 13፡26 እና በኢያሱ 2፡23 መካከል ምን ልዩነት ታያለህ? ሪፖርቱ ለእርሱ ብቻ እንዲመጣ ማድረጉ ለኢያሱ ምን ይጠቅመዋል ብለህ ታምናለህ?
8. ከረጅም ዘመናት በፊትም ሆነ በቅርቡ ጌታ የረዳህ ነገሮች ዛሬ ከፊትህ ለተደቀኑት ችግሮችህ ምን ያህል የእግዚአብሄርን ታማኝነት ያሳስቡሃል? ትናንትና የረዳህ አምላክ የማይለወጥ በመሆኑ ነገም እንደማይጥልህ ቃል ገብቷል፡፡

# ጥናት አምስት (ኢያሱ 3፡1-17)

የጥናት ዓላማ፡ አምላካችን በምንገባባቸው አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ አስቀድሞ እርሱ እንደሚገባና እስከምንወጣ ድረስም ራሱን እንደማያስወጣ በማወቅ እንድንበረታታ ለማድረግ፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹እነሆ፤ የምድር ሁሉ ጌታ የቃል ኪዳኑ ታቦት ቀድሟችሁ ወደ ዮርዳኖስ ይገባል፡፡ …እስራኤል በሙሉ ፈጽመው እስኪሻገሩ ድረስ በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል በደረቁ ምድር ላይ ቀጥ ብለው ቆመው ነበር፡፡›› ኢያሱ 3፡11, 17

1. ኢያሱ 3፡1-17 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-4 ውስጥ የጦሩ አለቆች ለህዝቡ የሰጧቸው መመሪያዎች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡
2. በቁ3 ‹‹…የቃል ኪዳን ታቦት ተሸክመው ስታዩ፤ ከሰፈራችሁ ተነስታችሁ ታቦቱን ተከተሉ፡፡›› በዚህ ክፍል የተሰጣቸው መመሪያ በእኛ ህይወት ምን ትርጉም ሊኖረው ይችላል ትላለህ?
3. ዘጸ 14፡15-16ትን አንድ ሰው ያንብብ፡፡ እግዚአብሄር ቀይ ባህርንና ዮርዳኖስን ለመክፈል የተጠቀመባቸውን መንገዶች የሚለያዩበትን ነገሮች ዘርዝር፡፡ ስለ እግዚአብሄር አሰራር ምን ልንማር እንችላለን?
4. ቁ4 ‹‹ካሁን በፊት በዚህ መንገድ ሄዳችሁ ስለማታውቁ›› ዘጻ 14፡15-16 ያየነው ክፍል ይህ አባባል ምን ማለት እንደሆነ ለመተርጎም እንዴት ሊረዳን ይችላል?
5. ‹‹…ወደ ታቦቱ አትቅረቡ፡፡›› ቁ4 የሚለው ሃሳብ ከአዲስ ኪዳን ከተሰነዘረው ሃሳብ በምን መንገድ እንደሚለይ በጥቅስ በመደገፍ አስረዳ፡፡
6. በ3፡9-11 መሰረት ለእስራኤላውያን የእግዚአብሄር በመካከላቸው መሆንና ጠላቶቻቸውን እንደሚረታላቸው ማረጋገጫ ሆኖ የተሰጣቸው ነገር ምንድነው? በእኛስ ህይወት ይህ እውነት በሥራ ላይ ሊተረጎም የሚችለው እንዴት ነው?
7. ቁ15 ‹‹ወቅቱም የመከር ጊዜ በመሆኑ፤ የዩርዳኖስ ወንዝ ሞልቶ ነበር›› አስቀድሞ ወይም ትንሽ ቆይቶ ማሻገር ሲችል እግዚአብሄር ለምን ወንዙ በሞላበት ጊዜ ማሻገር ፈለገ?
8. የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙት ወደ ወንዙ ለመግባት የመጀመሪያ ለመውጣት ደግሞ የመጨረሻ እንደሆኑ በቀ6 እና 17 ላይ እናያለን(ማለትም እግዚአብሄር ሲጀመር እስኪጨረስ ከነርሱ ጋራ ነበረ)፡፡ በፊት ለሚደቀኑብህ ችግሮች ይህንን ማወቅህ ምን ያህል ይረዳሃል? በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ስትሆን ይህንን ሃሳብ ወደ ልብህ እንዲያመጣ ጌታን ለምን?

# ጥናት ስድስት (ኢያሱ 4፡1-24)

የጥናት ዓላማ፡ ከልጆቻችንን የሚሰነዘሩትን ጥያቄዎች ሁሉ የእግዚአብሄርን ታላቅነትና ድንቅ ሥራ የምናስተምርባቸው ምቹ መድረኮች አድርገን ልንጠቀምባቸው እንደሚገባን ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ልጆቻችሁ ወደፊት፤ እነዚህ ድንጋዮች ምንድናቸው? ብለው አባቶቻቸውን ቢጠይቁ…››

1. ኢያሱ 4፡1-24 ያለው በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-3 ውስጥ እግዚአብሄር ለኢያሱን ያለው ነገር ምን ነበረ?
2. አስራ ሁለቱን ድንጋዮች እንዲያነሱ በእግዚአብሄር የተጠቀሙት ወደየት ነበረ? እግዚአብሄር ካህናቱ የቆሙበት ሥፍራ ላይ ማተኮሩ ለምንድነው ብለህ ትገምታለህ?
3. ቁ6 ‹‹ይህም በመካከላችሁ ምልክት…›› ቁ7 ‹‹የዘላለም መታሰቢያ›› ይህንን የሚያህል ድንቅ ነገር ማን ይረሳልና ነው እግዚአብሄር ምልክትና መታሰቢያ የፈለገው?
4. ኢያሱ 4፡6-7 በማንበብ ለምንድነው እግዚአብሄር ዛሬ በእኛ ህይወት ከሚካሄደው ነገር ባሻገር አርቀን እንድንመለከት ይፈልጋል ማለት የምንችለው?
5. በቁ12-13 ላይ የሰፈረው ሃሳብ ቃል ኪዳንን ስለማክበር በምን መንገድ እንደሚያስተምረን አስረዳ፡፡
6. በቁ21-22 ላይ በተለይ የልጆችን ጥያቄ አስመልክቶ የሚሰነዘረው ወደማን ነው? ከዚህ ምን መረዳት እንችላለን?
7. ኢያሱ 22-24ትን በማንበብ እግዚአብሄር ዮርዳኖስንና ቀይ ባህርን ያደረቀባቸው ምክንያቶች አንድ አይነት እንደሆኑ እንረዳለን፡፡ እነዚህ ሁለት ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡
8. የእግዚአብሄርን ማንነትና ድንቅ ሥራውን ለልጆች ባለማስተላለፍ ምን ጉዳት ታያለህ? ለልጆችህ የእግዚአብሄርን ነገር ለማስተላለፍ ምን ያህል ጥረት አድርገሃል? እግዚአብሄር ታላቅነቱን ማወቅና ማውራት በእኛ ብቻ እንዲቆም ስለማይፈልግ ለልጆችህ አስተላልፈው፡፡

# <u>ጥናት ሰባት (ኢያሱ 5፡1-15)</u>

የጥናት ዓላማ፡ ከባድ አደጋና ችግር ሊያስከትልብን እንደሚችልም እያወቅን እንኳን የአምላካችንን ትዕዛዝ መታዘዝ እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ስለዚህ ኢያሱ የባልጩት መቁረጫ አዘጋጅቶ ጊብዓዝ ዓረሎት በተባለ ሥፍራ እስራኤላውያንን ገረዛቸው፡፡›› ኢያሱ 5፡3

1. ኢያሱ 5፡1-15 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ ሲሆን የምናየው ነገር ምንድነው? እግዚአብሄር ዮርዳኖስን ካደረቀበት ምክንያቶች አንደኛው ተፈጻሚነት አግኝቷል የሚያሰኘን ምንድነው?
2. የእስራኤል ህዝብ ግርዛት ስላስፈለገበት ምክንያት በቁ4-8 ላይ የተሰጠው ሃሳብ ምን እንደሆነ በዝርዝር አስረዳ፡፡
3. በአንተ አመለካከት ግርዛትን ለማከናወን አሁን ያሉበት ሁኔታ ጊዜው ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን?
4. ታዲያ የነበሩበት ሁኔታ ለመግረዝ ጥሩ አልነበረም ካልን፤ ኢያሱ ሁኔታውን አልተረዳም ማለት ነው ወይ? ወይስ ይህንን ለማድረግ ምን ምክንያት ይኖረዋል ትላለህ?
5. በዚህ ክፍል መሰረት መና መብላት ያቆሙት መቼ ነው? በመናው መቆም የሚሰማቸው ስሜት ምን ይሆናል ብለህ ትገምታለህ? ለምን ይህንን ልትል እንደቻልክ አስረዳ፡፡ ዘኁ 11፡4-6ትን ማንበብ ህንን ጥያቄ ለመመለስ ይረዳል፡፡ በእኛ ህይወት አስቸጋሪ ጊዜን ልናልፍባቸው ስለሚሰጡን በረከቶች ሊሆኑ የሚችሉ ጥቂት ምሳሌዎች በመስጠት ተነጋገሩባቸው፡፡
6. በቁ13-15 ላይ ኢያሱ ለተገለጠለት ሰው ያቀረባቸው ሁለት ጥያቄዎች ምን እንደነበሩ ከነመልሳቸው ተናገር፡፡ በተለይ ለሁለተኛው ጥያቄ የተሰጠው መልስ ለጦርነት ለሚዘጋጅ ሰው የጦር ስልት ሊነገረው ሲገባ የዚህ ዓይነት መልስ መስጠቱ ምን ያስተምረናል?
7. ኢያሱ ጠላቶቹ ከፊት ለፊቱ እንዳሉ እያየ (ቁ8) የእግዚአብሄርን የመግረዝ ትዕዛዝ ለመታዘዝ መወሰኑ ምን ዓይነት ትምህርት ይሰጥሃል? ኢያሱ በገጠመው ሁኔታ ውስጥ ራስህን ብታገኝ ለእግዚአብሄር ሃሳብ ለመታዘዝ ምን ያህል ዝግጁ ነህ?

# ጥናት ስምንት (ኢያሱ 6፡1-27)

የጥናት ዓላማ፡ በእያንዳንዱ አማኝ ህይወት ጦርነት እንዳለና ለሁሉም ደግሞ የተሰጠው ዋነኛው የጦር ስልት በእግዚአብሄር አሸናፊነት ላይ ሙሉ በሙሉ የመደገፍ ምስጢር እንደሆነ ለመማር፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ይህንን ጦርነት የምትዋጉት እናንተ አይደላችሁም፣ ይሁዳና ኢየሩሳሌም ሆይ ቦታ ቦታችሁን ያዙ፣ ጸንጻችሁ ቁሙ፣ እግዚአብሄር የሚሰጣችሁንም ማዳን እዩ፡፡›› 2ኛ ዜና 20፡17

1. ኢያሱ 6፡1-27 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ4-5 እና ቁ6-10 ውስጥ እግዚአብሄር ለኢያሱ የሰጠው መመሪያዎች ምን ምን እንደነበሩ በዝርዝር ተናገር፡፡
2. በተራ ቁጥር 5 ላይ ባየነው ክፍል ውስጥ ኢያሱ የሚናገረው በጣም እርግጠኛ ሆኖ ነው፡፡ ይህንን ያህል ዓይነት እርግጠኛ እንዲሆን ያደረገው ነገር ምንድነው?
3. በቁ10 ላይ ኢያሱ ለህዝቡ ያስተላለፈው ትዕዛዝ በአንተ አስተያየት ለመፈጸም ከባደ ወይስ ቀላል ነው ብለህ ትገምታለህ? ለምን?
4. 6፡16-19 በኢያሪኮ ከተማ ውስጥ በሚገኝ ነገር ላይ መወሰድ ስላለበት እርምጃ የተነገራቸው ምንድነው? በዚህ ትዕዛዝ ውስጥ እንዳይጠቃለል የተነገረው ነገርስ ምንድነው?
5. ቁ22-23 ትን ስናነብ በረዓብ ቤት ውስጥ የነበረ ማንኛውም ሰው ከጥፋት አምልጧል፡፡ ይህ ሁኔታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚያስታውስህን ታሪክ/ኮች ተናገር፡፡
6. ቁ2 ‹‹ኢያሪኮን ከንጉሷና ከተዋጊዎችዋ ጋር በእጅህ አሳልፌ ሰጥቼሃለሁ፤፤›› ይህ ሰጥቼሃለሁ የሚለው ሃሳብ የሚያስገነዝበን አንድ ነገር ቢኖር ምንድነው ትላለህ?
7. በዚህ ምዕራፍ 6 ውስጥ ከእግዚአብሄርና ከኢያሱ ቀጥሎ በብዛት ተጠቅሶ የምናየው ስም የማን ስም ነው? ይህችን ሴት እግዚአብሄር ያከበረበት ምክንያት ለምን ይመስልሃ?
8. የጦር አበጋዙ በቁ2-5 የሰጠው ትዕዛዝ ምን ያህሉን ታዘዋል? ትዕዛዙ በአጠቃላይ በምን ላይ ያተኮረ ነበረ ትላለህ?
9. 2ኛ ዜና 20፡15፣ 20፣17 መዝ 46፡10ትንና ኤፌ 6፡12ትንና የመሳሰሉትን በማንበብ በአንተ ህይወት ውስጥስ ለሚነሳው ጦርነት እግዚአብሄር የሰጠህ የውግያ ስልት ምንድነው ትላለህ? ምን ያህል ይህንን የጦር ሥልት በሥራ ላይ ተፈጻሚ ታደርጋለህ?

# ጥናት ዘጠኝ (ኢያሱ 7፡1-26)

የጥናት ዓላማ፡ የሃጥያት ውጤት ሃጥያተኛውን ብቻ የሚጎዳ ሳይሆን ብዙዎች በአንድ ሃጥያት የተነሳ ቤተሰብ፤ ቤተክርስትያን አንዳንዴም ሃገር ሊጎዳ እንደሚችል ለማስገንዘብ።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ከዚያም እስራኤል በሙሉ በድንጋይ ወገሩት፤ የቀሩትንም እንደዚሁ ከወገሩ በኋላ በእሳት አቃጠሏቸው።›› ኢያሱ 7፡25

1. ኢያሱ 7፡1-26 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-5 ውስጥ የሰፈረውን ሃሳብ በአጭሩ ጠቅለል በማድረግ የሆነውን ሁኔታ ተናገር።
2. በተለይ ቁ2 ትን ስንመለከት ኢያሱ ያደረገው ነገር ምንድነው? በአንተ ግምት ይህንን ታክቲክ የተጠቀመበት ምክንያት ለምንድነው ተላለህ?
3. ጋይን ሰልለው የተመለሱት ሰዎች ከሪፖርት አሰጣጣቸው ምን ትረዳለህ?
4. ቁ5 ‹‹የህዝቡ ልብ ቀለጠ እንደውሐም ፈሰሰ›› የህን አነጋገር ቀድሞ ለማን ጸሐፊው የተጠቀመበት? አሁንስ በማን ላይ ነው ተፈጻሚ የሆነው? ለምን?
5. ከቁ6-9 ላይ ኢያሱና የህዝቡ ሽማግላች ምን ሲያደርጉ ነው የሚታዩት? በዚህ ክፍል የኢያሱ ሶስት ጥያቄዎች ምን ምንድናቸው?
6. ለኢያሱ ጥያቄ የእግዚአብሄር የመጀመሪያ አጭር መልሱ ምን ነበረ? እስራኤል ስለተሸነፈበት ምክንያት እግዚአብሄር በቁ10-11 ውስጥ አድርገዋል በማለት የሚዘረዝራቸውን ስድስት ነገሮች ተናገር።
7. ከቁ13-15 ውስጥ ምናልባት ለአካን የንስሃ ጊዜ ተሰጥቶት አልተጠቀመበትም ሊያሰኝን የሚችል የትኛው አረፍተ ነገር ነው?
8. በአካን ሃጥያት ምክንያት የተጎዱ ሰዎችን ዘርዝር።
9. ሃጥያትህ ከአንተ አልፎ ሌሎች ብዙዎችን ሊጎዳ እንደሚችል ምን ያህል ተረድተሃል? ከዚህ ትምህርት በውስጥህ የቀረ ነገር ካለ አካፍል።

# ጥናት አስር (ኢያሱ 8፡1-35)

የጥናት ዓላማ፡ አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሄር ሰራዊት/አማኝ ለጊዜው የተሸነፈና ድል የተነሳ ቢመስልም፤ እግዚአብሄር ለመጨረሻው ድል ለማዘጋጀት የሚጠቀምበት ስትራተጂ እንጂ በመጨረሻ ድሉ የእርሱ እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ኢያሱና እስራኤል በሙሉ ድል የተመቱ መስለው በመታየት ወደ ምድረበዳው ሸሹ፡፡›› ኢያሱ 8፡15

1. ኢያሱ 8፡1-35 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 እና በቁ 2 ላይ ኢያሱ እንዲያደርግ የተጠየቃቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡
2. ምዕራፉ ገና ሲጀምር ኢያሱን ‹‹አትፍራ፤ አትደንግጥ›› በማለት ነው፡፡ ለምንድነው ይህንን ቆራጥና በእምነት የተሞላ ሰው የዚህ አይነት ማደፋፈሪያ ያስፈለገው? ሐጥያት ሊያስከትል ስለሚችለው ከዚህ ክፍል ምን እንማራለን? ስለ እግዚአብሄር ምህረትስ?
3. ቁ3-4 ትን ስታነብ ኢያሱ እግዚአብሄር እንደታዘዘ የሚያሳዩህን ሁለት ሃሳቦች ተናገር፡፡
4. በቁ2 ላይ ‹‹በዚህ ጊዜ ግን›› የሚለውን አነጋገር ጸሐፊው ሲጠቀም ከየትኛው ጊዜ ጋራ ለማነጻጸር ፈልጎ ይመስልሃል?
5. በቁ15 ላይ ኢያሱና ህዝቡ የሸሹበት ምክንያት ለምን ነበረ? የዚህ የጦር ስልት ምንጩ ማን ነበረ?
6. እግዚአብሄር በጋይ የተጠቀመበት የድል መንገድ በኢያሪኮ ከተጠቀመበት የድል መንገድ በምን እንደሚለይ ተናገር፡፡ ከእነዚህ ሁለት ዓይነት የድል መንገዶች ምን ልንማር እንችላለን?
7. በጋይ ላይ ድልን ከተቀዳጁ በኂላ ያደረጉት የመጀመሪያ ነገር ምን ነበረ? ከዚህ ድርጊታቸው ምን እንደምትማር ተናገር፡፡
8. በ8፡30-35 ያለውን ሃሳብ ለመረዳት በዘዳ 11፡29 እና በዘዳ 27፡12-15 ያሉት ክፍሎች ሊረዱ እንደሚችሉ ተናገር፡፡
9. መሸሻቸውን ሲያዩ በቁ16 ላይ ጠላቶቻቸው ያደረጉት ምንነበረ? ጠላት ኢየሱስን ገደልኩ ብሎ መጨፈሩ እግዚአብሄር ለሰው ልጆች ያዘጋጀው የደህንነት መንገድ መሆኑን ሳይረዳው መሆኑ ዛሬም ጠላትህ ያሸነፈህ መስሎት ሰልፉን ቢጨምርም ድሉ በመጨረሻው የአንተ መሆኑን መዘንጋት አይገባህም፡፡

# <u>ጥናት አስራ አንድ (ኢያሱ 9፡1-27)</u>

የጥናት ዓላማ፡ አማኝ በእግዚአብሄር ፊት የሚገባው ቃል ኪዳን እንዲያው ተራ ንግግር እንዳልሆነና እስከመጨረሻው መጠበቅ የሚኖርበት ነገር እንደሆነ ከእስራኤላውያን ህይወት ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ነገር ግን መሪዎቹ ሁሉ ለማህበሩ እንዲህ ሲሉ መለሱ፤ በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሄር ስም ስለማልንላቸው፣ አሁን ጉዳት ልናደርስባቸው አንችልም›› ኢያሱ 9፡19

1. ኢያሱ 9፡1-27 ያለው በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 ውስጥ የሚካሄደው ምን እነደሆነ ተናገር፡፡ በዚህ ቁጥር ላይ ያሉትን ነገሥታት በዘጸ 23፡23 ካሉት ጋራ አነጻጽረህ ተመልከት፡፡
2. ኢያሱ 5፡1-2 ላይ እነዚህ ነገሥታት ልባቸው እንደቀለጠና እስራኤልን ለመውጋት ድፍረት እንዳጡ ይነግረናል፡፡ ታዲያ ምን የተለየ ነገር አግኝተው ነው ዛሬ ድፍረቱን ያገኙት? ከዚህ ሁኔታ ምን ልንማር እንችላለን?
3. በቁ3-6 ውስጥ የጋይ ሰዎች ያደረጉት ምን ነበረ? ለምንድነው ከሩቅ መምጣታቸውን ማረጋገጥ የፈለጉት?
4. በኢያሱ 9፡7 እና 11፡19 መሰረት በገባዖን የሚኖሩት እነማን ነበሩ? ዘጸ 23፡32 ስለ እነዚህ ሰዎች ምን ይነግረናል?
5. ቁ7-13 ላይ የተካሄደውን ሃሳብ አጠር አድርገህ ተናገረው፡፡ የእነዚህን ሰዎች ሁኔታ ከረአብ ጋራ በማነጻጸር የሚመሳሰሉበትን መንገዶች ዘርዝር፡፡
6. ቁ9-10 ላይ እግዚአብሄር ቀድሞ ያደረገውን ነገሮች ሲዘረዝሩ በቅርቡ በኢያሪኮና በጋይ ላይ ያደረጋቸውን አልተናገሩም፤ ይህ ለምን ይመስልሃል?
7. በ7-16 ውስጥ ለቀረበላቸው የቃል ኪዳን መግባት ጥያቄ የእስራኤል መሪዎች ያደረጉት ነገር ምን ነበረ? ያላደረጉት ነገር ምን እንደነበረ ተናገር፡፡ መሳሳታቸውንስ ያወቁት መቼ ነው?
8. 9፡19ንና 2ኛ ሳሙ 21፡1-3 በማንበብ እግዚአብሄር ቃል ኪዳንና መጠበቅ በተመለከተ ስላለው አመለካከት ምን ትረዳለህ? በእግዚአብሄር ሥም የምትገባውን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ ምን ያህል ትተጋለህ? ቃል ኪዳን ለመግባት አትቸኩል፣ ከገባህ ግን ተፈጽመው ዘንድ ትጋ፡፡ መክብብ 54-፡5 ትን መመልከት ይረዳል፡፡

# ጥናት አስራ ሁለት (ኢያሱ 10፡1-28)

የጥናት ዓላማ፡ የገባዖን ሰዎች የተገባላቸውን ቃል ኪዳን በሚገባ እንደተጠቀሙበት፤ እኛም ጠላት በህይወታችን ለሚያመጣው ማናቸውም ነገር የቃል ኪዳኑን ጌታ መጥራት የመጀመሪያው ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባን ነገር እንደሆነ ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹የገባዖን ሰዎችም...ሃይላቸውን አስተባብረው ተሰልፈውብናልና እኛን ባሪያዎችህን አትተወን፣ እርዳን፣ ፈጥነህ በመድረስም አድነን›› በማለት ላኩበት፡፡ ኢያሱ 10፡6

- ኢያሱ 10፡1-28 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-4 ውስጥ አዶኒጼዴቅና ህዝቡ የደነገጡባቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምን ነበሩ? ከዚህ ክፍል ስለ ገባዖን ከተማ የምንረዳቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡
- ከላይ ባየናቸው ቁጥሮች ውስጥ የገባዖን ሰዎች ከእግዚአብሄር ህዝብ ጋራ ቃል ኪዳን መግባታቸው ያስከተለባቸው ነገር ምን ነበረ? ይህንን ሁኔታ ሰው ጌታን ለመከተል ቃል ኪዳን ሲገባ ከሚከሰተው ሁኔታ ጋራ በማነጻጸር ተናገር፡፡ የገባዖን ሰዎች ለሁኔታው ምላሻቸው ምን እንደነበረና ከምላሻቸው እኛ ምን ልንማር እንደምንችል ተወያዩበት፡፡
- ቁ7-11ድን ስታነብ ኢያሱና እግዚአብሄር የየራሳቸውን ድርሻ ተወጥተዋል ሊያሰኙን የሚያስችሉንን ሃሳቦች ዘርዝር፡፡ ከዚህ ምን ትምህርት መቅሰም እንችላለን?
- ም6 በኢያሪኮ፣ ም8 በጋይና እንዲሁም ደግሞ በዛሬው ምንባብ ውስጥ እስራኤልን ለመርዳት የእግዚአብሄር ተሳትፎ በምን መንገድ እንደሚመሳሰልና በምን መንገድ ደግሞ እንደሚለያይ በማነጻጸር ተናገር፡፡
- ቁ9-11 ያለውን ክፍል ስታይ ጦርነቱ ከኢያሱ ጋራ መሆኑ ቀርቶ ከእግዚአብሄር ጋራ ነበረ ሊያሰኙ የሚችሉት ሃሳቦች የትኞቹ ናቸው?
- በቁ12-15 ላይ እግዚአብሄር ያደረገው ተአምር በተለይ ፀሐይንና ጨረቃን ለሚያመልክ ለዚህ ህዝብ የሚሰጠው ትምህርት ምን ይሆናል ትላለህ?
- ቁ22-26 ኢያሱ በነገስታቱ ላይ ጭካኔ የተሞላበት የሚመስል ነገር ሲያደርግ ይታያል፡፡ ለዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል የምትላቸውን ቢያንስ ሁለት ሃሳቦች ተናገር፡፡
- የዛሬውን ምንባብ በማየት የገባዖንን ሰዎች ብልህ ሊያሰኛቸው የሚችል ምን ነገር ታያለህ? አንተስ ቃልኪዳን ያለህ ሰው እንደሆንክ ተረድተሃል ወይ? ቃልኪዳንህንስ ምን ያህል ትጠቀምበታለህ?

# ጥናት አስራ ሶስት (ኢያሱ 14፡1-15)

የጥናት ዓላማ፡ ሁኔታዎቹ ከባድና አስቸጋሪ እንደሆኑ እያወቅን እንደ ካሌብና አብርሃም (ሮሜ 4፡18) አምላካችን ከሁኔታዎቹ በላይ እንደሆነ በማመን በገባልን የተስፋ ቃል ላይ መቆምን ለመማር፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ኤናቃውያን በዚያ እንደነበሩ ከተሞቻቸውም ታላላቅና የተመሸጉ እንደሆኑ… ሆኖም ልክ እርሱ እንዳለው በእግዚአብሄር እርዳታ አሳድጄ አወጣቸዋለሁ፡፡›› ኢያሱ 14፡12

1. ኢያሱ 14፡1-15 በአንድነት ይነበብ፡፡ ለእስራኤል ርስታቸውን በማከፋፈል የተሳተፉት እነማን ነበሩ? ርስቱን የተከፋፈሉት በምን መሰረት ነው?
2. በዚህ ርስት ክፍፍል ውስጥ የሌሉበት እነማን ነበሩ? እነዚህ ከዚህ ርስት ያልተካፈሉበት ምክንያት ምን ነበረ?
3. በቁ6-9 ባለው ክፍል ውስጥ፣ ካሌብ የፈለገውን ርስት ለመቀበል ኢያሱን ሲያነጋግር ሃሳቡን የጀመረውና መሰረት ያደረገው ምኑን ነበረ? ከዚህ አደራረጉ ምን ልንማር እንችላለን?
4. በቁ6-9 ውስጥ ካሌብ ስለራሱ የተናገራቸውን ነገሮች በሙሉ በመዘርዘር ተናገር፡፡ ስለራሱ የተናገረው ታሪክ በሙሉ እውነት ለመሆኑ ሊመሰክር የሚችል ሰው ማን አለ?
5. ቁ7 ላይ ‹‹እኔም ትክክለኛ ማስረጃ ይዤለት መጣሁ›› ሲል እውነተኛ ማስረጃ ማለቱ ነው ወይ? እውነተኛ ማለቱ ከሆነ ሌሎቹ አስሩስ ስለሰለሉት ሃገር የተናገሩት እውነት አልነበረም ወይ? ታዲያ በካሌብና አስሩ ባመጡት ማስረጃ መካከል የነበረው ልዩነት ምን ነበረ?
6. ካሌብስ በ10-12 ውስጥ ለዚህች ምድር መብቃቱን በምን ምክንያት ነው ይላል? ከዚህ ምን መማር እንችላለን?
7. ካሌብ እግዚአብሄርን በፍጹም ልቡ እንደተከተለ የተናገሩት እነማን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡
8. በዘኁ 13፡30 የምታየው ካሌብ በዚህ ክፍል ከምታየው ካሌብ የሚመሳሰልበትና የሚለይበትን ነገሮች ተናገር፡፡
9. ከካሌብ ህይወት አንድ የምታደንቀውና በህይወትህ እንዲሆን የምትናፍቀው ነገር ምንድነው? አምላክህን ምን ያህል ከሁኔታዎችህ አስበልጠህ ማየት ተለማምደሃል? በካሌብና በአስሩ ሰላዮች መሃል የነበረው ልዩነት ሁኔታውን ወይም እግዚአብሄርን ማስበለጥ እንደነበረ፤ የካሌብን ፈለግ መከተል ከፈለክ ተኩተትህ በአምላክህ ላይ ይሁን፡፡

## (ሀ) ጥናት አስራ አራት (ኢያሱ 17፡1-18)

የጥናት ዓላማ፡ በክርስትና ህይወታችን ለማደግ ወይም እግዚአብሄርን ደስ የሚያሰኘውን ለማድረግ ስናስብ፤ ካሰብንበት ግብ ለመድረስ መክፈል የሚያስፈልጉንን መስዋዕቶች እንደሚኖሩና ያንንም ለማድረግ ፈቃደኞች መሆን እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹…ነገር ግን ደን የለበሰው ኮረብታማው አገር የእናንተ ነው፤ ሄዳችሁ መንጥሩት፣ ዳር ድንበሩ ሁሉ የእናንተ ይሆናል፡፡›› ኢያሱ 17፡18

1. ኢያሱ 17፡1-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ3 መሰረት ስለ ሰለጸዓድ የምናውቃቸው እውነቶች ምን ምንድናቸው? የሰለጸዓድ ሴቶች ልጆች የገጠማቸው ሁኔታ ምን ነበረ? ስለሁኔታውስ ምን አይነት እርምጃ ወሰዱ?
2. እነዚህ ሴቶች ወደ ኢያሱና ነገሩ ወደሚመለከታቸው ከመሄድ ይልቅ ሊወስዱ የሚችሏቸው ሌሎች ምን አቅጣጫዎች ሊኖሩ ይችላሉ ብለህ ታምናለህ? ከዚህ አድራጎታቸውስ ምን መማር እንችላለን?
3. ለሰለጸዓድ ሴቶች ልጆች በእውቀትም ሆነ ባለማወቅ አጥተውት የነበረውን ርስታቸውን ለማግኘት የጠቀማቸው አንዱና ዋነኛው ነገር በአንተ አመለካከት ምንድነው ትላለህ?
4. በቁ4 ላይ የሰለጸዓድ ልጆች ባቀረቡትና በቁ14 ላይ የዮሴፍ ዘሮች ለኢያሱ በቀረቧቸው ጥያቄዎች መሃል ምን ልዩነት ታያለህ? በቁ4 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ ምላሹን ለመስጠት ለኢያሱ አስቸጋሪ ያልሆነበት ምክንያት ለምንድነው ትላለህ?
5. በቁ16 ላይ የዮሴፍ ዘሮች የሚያሳዩት አመለካከት ካሌብ በኢያሱ 14፡12 ላይ ከነበረው አመለካከት የሚለየው በምን መንገድ ነው?
6. የዮሴፍ ዘሮች አንድ ድርሻ አይበቃንም(ቁ14) ላሉት የኢያሱ መልስ ምን ነበረ? በቁ16 ላይ እነዚህ ሰዎች ለኢያሱ የሚሰጡት ምላሽ ምን ብለው ነው? ተጨማሪ ድርሻ ፈልገው ነገር ግን የሚያስከፍለውን መስዋዕትነት አለመፈለጋቸውን ከእኛ ህይወት ጋራ በማነጻጸር ተነጋገሩበት፡፡
7. የእነዚህ ሰዎች ፍርሃት የኢያሱን ሃሳብ አስቀይሮታል ወይ? ችግር ብለው ላቀረቡት ነገር የኢያሱ መፍትሄው ምን ነበረ?
8. የዮሴፍ ዘሮች ተጨማሪ ድርሻ መጠየቃቸው ስህተት ነበረ ወይ? ያልተረዱት አንድ ነገር ምን ነበረ? አንተስ በክርስትና ህይወትህ ልትደርስበት የምትፈልገው ግብ አለህ ወይ? በክርስትና ማናቸውም እድገት ያለመስዋዕትነት የለምና ልብህ ለዚያ ሊዘጋጅ ያስፈልጋል፤፤

## (ለ) ጥናት አስራ አራት (ኢያሱ 17፡1-18 ዘኍ 27፡1-8)

የጥናት ዓላማ፡ ትክክል እንዳልተሰራ ወይም እንደተበደልን የሚሰማን ነገር ሲኖር በውስጣችን ይዘን ወደ ሃሜትና ወደ ማጉረምረም ከመሄድ ይልቅ ወደሚመለከተው ግለሰብ በመሄድ ማነጋገር የተሻለ ውጤት ሊያስገኝ እንደሚችል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹እነርሱም ወደ ካህኑ ወደ አልዓዛር፣ ወደ ነዌ ልጅ ወደ ኢያሱና ወደ መሪዎቹ ቀርበው… እግዚአብሄር ሙሴን አዞታል አሏቸው፡፡›› ኢያሱ 17፡4

1. ኢያሱ 17፡1-18 እና ዘኍ 27፡1-8 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ3 መሰረት ስለ ሰለጳዓድ የምናውቃቸው እውነቶች ምን ምንድናቸው? የሰለጳዓድ ሴቶች ልጆች የገጠማቸው ሁኔታ ምን ነበረ? ስለሁኔታውስ ምን አይነት እርምጃ ወሰዱ?
2. ዘኍ 27፡1-4 ያለው ክፍል የሁኔታውን አጀማመር በግልጽ ይናገራል፡፡ ይህንን ክፍል በመመርኮዝ የነገሩ አነሳስ ምን እንደነበረ በራስህ ቋንቋ አስረዳ፡፡
3. ሙሴ በዘኍልቁ ላይ ስናነብ ጥያቄው ሲቀርብለት ያደረገው ነገር ምን ነበረ? ኢያሱ ወዲያው የጠየቁትን ሲያደርግ እናያለን፡፡ ኢያሱ ለምን ጥያቄውን እንደሙሴ ወደ እግዚአብሄር አልወሰደውም? ከዚህ እኛ ምን ልንማር እንችላለን?
4. እነዚህ ሴቶች ወደ ኢያሱና ነገሩ ወደሚመለከታቸው ከመሄድ ይልቅ ሊወስዱ የሚችሏቸው ሌሎች ምን አቅጣጫዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ተናገር፡፡
5. ለሰለጳዓድ ሴቶች ልጆች ርስታቸውን ለማግኘት የጠቀማቸው ዋናው ቁልፍ ነገር በአንተ አመለካከት ምንድነው ትላለህ?
6. በቁ4 ላይ የሰለጳዓድ ልጆች ባቀረቡትና በቁ14 ላይ የዮሴፍ ዘሮች ለኢያሱ በቀረቧቸው ጥያቄዎች መሃል ምን ልዩነት ታያለህ? በቁ4 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ ምላሹን ለመስጠት ለኢያሱ አስቸጋሪ ያልሆነበት ምክንያት ለምንድነው ትላለህ?
7. ዘኍ 27፡8ትን ስታይ የእነዚህ ሴቶች ድርጊት ምን ያስከተለው ነገር ታያለህ? ጥቂት ሰዎች ለእግዚአብሄር ቃል ቦታ በመስጠታቸው ምክንያር ሊከሰት ስለሚችለው ነገር ምን ትማራለህ?
8. የሰለጳዓድ ልጆች የወሰዱት እርምጃ ጥበብ የተሞላውና ድፍረት የሚጠይቅ ጉዳይ ነበረ ሊያሰኙን ምን ምክንያቶች ይታዩሃል? አንተስ ትክክል ያልሆነ ነገር ስታይ የምትወስደው እርምጃ ምንድነው? የሰለጳዓድን ሴቶች ልጆች ምሳሌነት መከተል ብልህነት ነው፡፡

# ጥናት አስራ አምስት (ኢያሱ 22፡1-34)

የጥናት ዓላማ፡ በወገኖቻችን ላይ አንድ የሆነ ነገር ስንሰማ አስቀድመን ከራሳቸው አፍ ስለሆነው ነገር ሳንሰማ የቃልም ሆነ የተግባር እርምጃ መውሰድ በኂላ ጸጸትና እፍረት እንደሚሆንብ ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፣ ለመናገር የዘገየ፣ ለቁጣም የዘገየ ይሁን፤ የሰው ቁጣ የእግዚአብሄርን ጽድቅ አያመጣምና፡፡›› ያዕ 1፡19-20

1. ኢያሱ 22፡1-34 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-3 መሰረት እነዚህ የሮቤል፣ የጋድና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ታዛዥነታቸውንና ታማኝነታቸውን ያረጋገጡት ለማን ነበረ? የነዚህን ሰዎች ታማኝነትቸውን የጎላ የሚያደርገው ኢያሱ ከጠቀሰው ሃሳብ ምን ትመለከታለህ?
2. በቁ4-5 ኢያሱ እነዚህን ሁለት ተኩል ነገዶች ሲያሰናብት የሰጣቸው ማስጠንቀቂያዎች ምን ምን እንደነበሩ በመዘርዘር አስረዳ፡፡
3. በቁ9-12 ላይ የተከናወኑት ነገሮች ምን ምንድናቸው? ይህ ግዙፍ መሰዊያ የተሰራበት ትክክለኛ ቦታ የት ነበረ?
4. ቁ13-14 ትን ስናነብ እስራኤላውያን ሁኔታውን ሲሰሙ የወሰዱት እርምጃ ምን ነበረ? ለዚህ ተልዕኮ የተመረጡትስ ሰዎች እነማን ናቸው? ዘኍ 25፡6-9ትን ስታነብ በተለይ ፊንሃስን ለዚህ ተልዕኮ ትክክለኛ ሰው ነው ሊያሰኝ የሚችል ምን ሃሳብ ታያለህ?
5. ቁ15-18 ባለው ክፍል ላይ የተካሄደውን ምን እንደነበረ ተናገር፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ስታይ፤ ያዕ1፡19 የሚናገረው ሃሳብ በተግባር ላይ አልዋለም ሊያሰኝን የሚችል ምን ነገር ታያለህ?
6. ለምንድነው የሮቤልና የጋድ እንዲሁም የምናሴ ነገድ እኩሌታ በቁ21-23 ውስጥ ሲናገሩ የሚቃጠል መስዋዕት ለማቅረብ አለመሆኑን አስረግጠው መናገር የፈለጉበት ምክንያት? ዘሌ 17፡3-4 ያለውን ማንበብ ይረዳል፡፡
7. ቁ24-28 መሰዊያው ስለተሰራበት ትክክለኛ ምክንያቱን ያሳየናል፡፡ ይህ ምክንያት ምን ነበረ? በቁ16 ላይ መልዕክተኞቹ ከተናገሩት ሃሳብ ጋራ ምን ያህል ተመሳሳይነት አለው ትላለህ? ቁ29 ኝን ስታነብ የእግዚአብሄርን ቃል አስመልክቶ ስለተከሰሱት ሰዎች ምን ትረዳለህ?
8. የእስራኤል ልጆች ካደረጉት ነገሮች ውስጥ የሚታይህን አንድ መልካምና አንድ መጥፎ የምትላቸውን ነገሮች ተናገር፡፡ አንድ ወሬ ስትሰማ አስቀድመህ የምትወስደው እርምጃ ምንድነው? አፍን ቸኩሎ መክፈት በኂላ እፍረትን ሊያመጣ ስለሚችል እርምጃ ከመውሰድህ አስቀድሞ ነገርን ማረጋገጥ ብልህነት እንደሆነ ከያዕ 1፡19-20 ተማር፡፡

# ጥናት አስራ ስድስት (ኢያሱ 23፡1-16)

የጥናት ዓላማ፡ ከአምስት መቶ አመታት በፊት ለአብርሃም የገባውን የቃል ኪዳን ለመፈጸም የታመነው አምላክ ዛሬም ጊዜው ይርዘም እንጂ የገባውን ቃል ኪዳን የሚፈጽም ታማኝ አምላክ እንዳለን አስረግጠን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹አምላካችሁ እግዚአብሔር ከሰጣችሁ መልካም ተስፋ ሁሉ አንዲቱን እንኳ እንዳላስቀረባችሁ፣ በፍጹም ልባችሁ በፍጹም ነፍሳችሁ ታውቃላችሁ፤ አንዱም ሳይቀር ሁሉም ተፈጽሟል፡፡›› ኢያሱ 23፡14

1. ኢያሱ 23፡1-16 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-2 ስለ እስራኤል ህዝብ የሚናገረው ምን ነገር አለ? ስለ ኢያሱስ ምን መረዳት ትችላለህ?
2. በቁ2 ላይ ኢያሱ ስለራሱ የሚናገረው እውነት ምንድነው? ለምንድነው ሰዎች የማይወዱት የእርጅና ነገር ለኢያሱ አሳፋሪና አስፈሪ ያልሆነበት ምክንያት?
3. ቁ3-5 ትን ስናነብ እግዚአብሔር ስለህዝቡ ስላደረጋቸውና ስለሚያደርጋቸው ነገሮች ምን እንረዳለን? እግዚአብሔር ስላደረገው ነገርስ በመረጃነት የሚያቀርበው ማንን ነው?
4. 6-8 ባለው ክፍል ውስጥ ኢያሱ የተናገራቸው ቃላቶች ምንጫቸው ከየት ይመስልሃል? ይህን የኢያሱ ማበረታቻና ማጽናኛ ስትመለከት ወደ አዕምሮህ የሚመጣው የአዲስ ኪዳን ጥቅስ ምንድነው?
5. በእነዚህ ሶስት ቁጥቶች ውስጥ(6-8) ኢያሱ እስራኤልን የሚያስጠነቅቃቸውን ነገሮች አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡ እነዚህን የተዘረዘሩትን ሁሉ በሁለት አጫጭር ዓተፍተ ነገሮች በመጠቅለል ተናገር፡፡
6. ቁ9-11 እግዚአብሔር ስላደረገላቸውና ስለሚያደርግላቸው ነገሮች ምን ይናገራል? ለዚህ ምላሽ የሚጠይቃቸውስ ነገር ምንድነው? አንተስ ይህንን ምላሽ ለመስጠት ምን ያህል ትተጋለህ?
7. ቁ12-13 በተለይ ያተኮረበት አንድ ሃጥያት ምንድነው ትላለህ? ይህንን በዚህ ዘመን ላለነው ተግባራዊ ስለሚሆንበት ሁኔታ በምሳሌ አስረዳ፡፡
8. ከቁ14ና15 ስለ እግዚአብሔር የተስፋ ቃል ምን እንማራለን? ያስተፈጸመ የምትጠብቀው አንድ ተስፋ ምን እንደሆነ ተናገር፡፡ ይህንንም ደግም እግዚአብሔር እንደተናገረው ይፈጽመዋል፡፡

# ጥናት አስራ ሰባት (ኢያሱ 24፡1-13)

የጥናት ዓላማ፡ የትውልድ ሐረጋችን በምንም ዓይነት የባዕድ አምልኮና እስራት የኖሩ ቢሆኑም እንኳን በእግዚአብሄር ታዳጊነት ከእርግማን ወደ በረከት የተጠራን ህዝብ የትውልዱ እርግማን ቆጥሮ ሊያገኘው እንደማይችል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ይዋሽ ዘንድ እግዚአብሄር ሰው አይደለም…እባርክ ዘንድ ትዕዛዝ ተቀብያለሁ፤ እርሱ ባርኳል እኔም ልለውጠው አልችልም፡፡›› ዘኍ 23፡19-20

1. ኢያሱ 24፡1-13 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁጥር 1-4 የሰፈረው ታሪክ ቢያንስ የስንት ዓመታቱን ታሪክ ነው የሚያጠቃልለው? በመጽሐፍ ቅዱሳችንስ ከየት ጀምሮ እስከ የት ያለውን ክፍል ነው የሚጨምረው?
2. በዚህ ክፍል መሰረት አብርሃም ከአያቶቹና ከቅድመ አያቶቹ የተለየ ሆኖ የተገኘው ከምን የተነሳ ነው? ክፍሉ እግዚአብሄር ለአብርሃም ስላደረጋቸው ነገሮች የሚናገረውን ዘርዝር፡፡ አብርሃምስ ለዚህ ያደረገው አስተዋጽዖ ምን ነበረ?
3. ቁ5-7 ያለው ክፍልስ ምን ያህል ዓመታትን የሚያጠቃልል ነው? በእነዚህ ዓመታት እግዚአብሄር ለህዝቡ አደረጋቸው ተብለው በዚህ ክፍል የተነገሩትን ጥቂቶቹን ዘርዝር፡፡
4. በቁ8-10 ውስጥ እግዚአብሄር ለህዝቡ ያደረጋቸው ሁለት ትላልቅ ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ለምንድነው እግዚአብሄር በለዓምን ለመስማት ያልፈለገው? ዘኍ 23ትን ማንበብ ይረዳል፡፡
5. በቁ11-13 ውስጥ በኢያሪኮ ከተማ ከተካሄደው ውግያ ከዚህ ክፍል የምናገኘው ተጨማሪ መረጃዎች ምን ምንድናቸው? በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ህዝቡ እንዲረዱት የፈለገውና እየተናገራቸው ያሉትን እውነቶችን ዘርዝር፡፡
6. ለምንድነው እግዚአብሄር ከመጀመሪያው ጀምሮ ያደረገላቸውን በቅደም ተከተል መናገር ያስፈለገው? ጸሐፊው በኢያሱ 24፡1-13 የተናገረውን ሃሳብ በአንድ አጭር አረፍተ ነገር ጨምቀህ ተናገር፡፡
7. ይህ በዛሬው ምንባብ የተዘረዘረው በረከት ሁሉ ከአብርሃም ጋራ የሚያያዘው በምን መንገድ ነው? በአብርሃም የትውልድ ሐረግ የነበረው ያ እርግማን የተሰበረው መቼ ነበረ?
8. የትውልድ እርግማን በሚል ሃሳብ ሰዎች ስለአንተም ሆነ ስለሌላ ሰው ሐሳብ ሲሰጡ ሰምተህ ታውቃለህ ወይ? እግዚአብሄር በክርስቶስ ኢየሱስ የባረከን ስለሆነ ዘኍ 23፡19-20 እንደሚነግረን እርሱ ባርኳል ማንም ሊለውጠው አይችልምና በዚህ ልትጽናና ይገባሃል፡፡

# ጥናት አስራ ስምንት (ኢያሱ 24፡14-33)

የጥናት ዓላማ፡ እግዚአብሄር ያደረገልንን ቸርነትና ምህረቱን ሁሉ በትክክል መረዳትና ማወቃችን እርሱን ለማገልገልም ሆነ ለማምለክ ትልቅ አስተዋጽዖ እንዳለው ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሄርን ደስ የሚያሰኝ ህያው መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሄር ርህራሄ እለምናችኋለሁ፡፡›› ሮሜ 12፡1

1. ኢያሱ 24፡14-33 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ14 ላይ ኢያሱ ህዝቡ እንዲያደርጉ የሚጠይቃቸውን ነገሮች ዘርዝር፡፡
2. በቁ1 ላይ ከሁሉ ይልቅ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል የምትለውን አንድ ቃል የትኛው ነው? ለምን ይህንን ለማለት ቻልክ?
3. በኢያሱ 24፡1-13 የእግዚአብሄርን ቸርነትና ለረጅም ዘመናት ያሳያቸውን ታማኝነት በዝርዝር እንዳሰፈረላቸው ተመልክተናል፡፡ የዛሬው ክፍል ደግሞ ሲጀምር እርሱ ላደረገላቸው ቸርነት ሊሰጡት በሚገባቸው ምላሽ ይጀምራል፡፡ ይህ ክፍል ከሮሜ 12፡1 ጋራ የሚመሳሰለው በምን መንገድ እንደሆነ አስረዳ፡ ከነዚህ ክፍሎች አቀራረብ የምትማረውን ነገር አካፍል፡፡
4. በቁ16-20 ላይ ለኢያሱ ጥያቄ የህዝቡ ምላሽ ምን ነበረ? ኢያሱስ የህዝቡን ምላሽ እንዴት ተቀበለው? ‹‹እግዚአብሄርን ልታመልኩ አትችሉም›› ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል?
5. በቁ21-24 በህዝቡና በኢያሱ መሃል የተካሄደውን ውይይት በራስ ቃላት ግለጽ፡፡ ቁ23 ላይ ያለው የኢያሱ አነጋገር ስለሰዎቹ ሁኔታ ምን ፍንጭ ይሰጠናል? አንተስ በህይወትህ ደባል ያደረከው ነገር ምንድነው? ራስን መመርመር አይከፋም፡፡
6. ቁ28-33 ባለው ክፍል ውስጥ የተጠቀሱት ሶስቱ የእግዚአብሄር አገልጋዮች እነማን ናቸው? ስለሶስቱ ሰዎች የተጻፈው ተመሳሳይ ነገር ምንድነው? ኢያሱ በዚህ ክፍል የተሰጠው የመጠሪያስ ምን ነበረ?
7. ኢያሱ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚጥረው ጥረት ምን ውጤት ለማግኘት ነው ትላለህ?
8. እግዚአብሄር በህይወታችን የሰራውንና ያሳየንን ምህረት በተረዳ ሰውና ባልተረዳ ሰው መሀል መታዘዝና እርሱን ብቻ ማምለክን አስመልክቶ ሊኖር የሚችለው ልዩነት ምን ይመስልሃል? የምታገለግለውና የምታመልከው የተደረገልህን ቸርነት በማሰብ ወይስ ግዴታህ ስለሆነ? በአገልግሎትህም ሆነ በአምልኮህ እንድትነቃቃ የተደረገልህን መለስ ብለህ አስብ፡፡